# "ዴሞክራሲን ከማግኘት ይልቅ፤ ጠብቆ ማቆየቱ ይከብዳል"

**(ክፍል አንድ)**

**አሜን ተፈሪ 01-22-18**

የኢትዮጵያ ህዝብ ለዘመናት በዘለቀ የፖለቲካ ሁከት እና ጦርነት የተቸገረ ህዝብ ነው፡፡ ይህ ችግር ሐገሪቱን ከከፋ የድህነት አዘቅት ውስጥ አስሮ ያቆያት ችግር ነው፡፡ ህዝቡም ይህ ችግር ተወግዶ የሰላም አየር ለመተንፈስ ሲመኝ ቆይቷል፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ በብዙ ቀውሶች ስትታመስ ዘመናትን የገፋችው ሐገሩ መረጋጋት አግኝታ፤ የደቀቀ ሕይወቱን መልሶ ለመገንባት እና ኑሮውን ለማሻሻል ሲመኝ ከርሞ-ባጅቷል፡፡ ይህን ምኞቱን ለማሳካት የሚያስችል (ምናልባትም በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ) ሊባል የሚችል ዕድል ባለፉት ሃያ ሰባት ዓመታት አግኝቷል፡፡ ይህ ልዩ ዕድል ሳይደናቀፍ ይበልጥ ጥንካሬ እና ጥልቀት እያገኘ መሄድ የሚችለው፤ ብዝሃነትን ከአንድነት ጋር አስተሳስረን መጓዝ ከቻልን ብቻ ነው፡፡

ኢትዮጵያ በውስጧ የሚገኙ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦችን ልዩነት በመዘንጋት ወይም እንደ ነገሩ በመያዝ ለችግር ብትዳረግም፤ የዳር እና የመሐል ሥፍራ የተሰጠው ባህል ይዛ ባደረገችው ያልተሳካ ጉዞ ውስጣዊ ሰላም ብታጣም፤ እንደ ሐገር የመቆየት ጥበብን ማዳበር እና አሁን ለተፈጠረው ፌዴራል ህብረት መሠረት ሊሆን የቻለ የህዝቦች ግንኙነትን መፍጠር ችላለች፡፡

ታዲያ እንደኛ ያሉ ህብረ ብሔራዊ የሆኑ ሐገራት በሚያካሂዱት የሐገር ግንባታ ጥረት ውስጥ ሁሌም የሚደቀነው ችግር፤ የብሔር ማንነትን ሳያጠፉ አንድነትን መፍጠር የሚቻለው እንዴት ነው የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ጥያቄ ምናልባትም ከሌሎች ሐገራት በተለየ ሁኔታ በኢትዮጵያ ልዩ ትርጉም የነበረው ጥያቄ ነበር፡፡ ይህን ጥያቄ በአግባቡ ለመመለስ ስትቸገር የቆየችው ሐገራችን፤ ከሁለት አስርት ዓመታት በፊት ለጉዳዩ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት ችግሩን ለመፍታት ሞክራለች፡፡ በዚህም ለልማት እና ለዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ሥራዎች ምቹ የሆነ የሰላም ሁኔታ እና ፌዴራላዊ የአስተዳደር ስርዓት መፍጠር ችላለች፡፡ በዚህም ባለፉት ሃያ ሰባት ዓመታት፤ በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ሊባል የሚችል የልማት፣ የሰላም እና የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ዕድል አግኝታለች፡፡

ሆኖም የተገኘውን ይህን ልዩ ዕድል ጠብቆ ለማዝለቅ፣ የብሔር ማንነት እና የብሔራዊ አንድነት ስሜት ተመጋጋቢ ሆነው፣ አንዱ አንደኛውን ባርኮ፣ ልዩነቱ አንድነትን ቀድሶ እና አጎልምሶ እንዲሄድ በማድረግ ረገድ የታዩ ጉድለቶችን ማስተካከል ይኖርብናል፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብ እንደ ማንኛውም ህዝብ ጭቆናን ይጠየፋል፣ ማንነቱም እንዲከበርለት ይፈልጋል፡፡ ለዚህም ታግሏል፡፡ ሰብአዊ መብቱ እና ነጻነቱ ያለ ገደብ እንዲከበርልት ይሻል፡፡ እንዲሁም መገነጣጠል የሚያመጣውን ከፍተኛ ችግር ጠንቅቆ ይረዳል፡፡ ስለዚህ ማንነቱ እንዲከበርለት ሲጠይቅ፣ በፌዴራላዊት ኢትዮጵያ ጥላ ሥር አንድነቱን ጠብቆ ለመኖር ወስኖ ነው፡፡

ገና ከማለዳው በሰኔ 1983 ዓ.ም በተካሄደው የሰላም ኮንፈረንስ ጎልቶ ይሰማ የነበረው የኢትዮጵያ ህዝብ ድምጽ፣ ‹‹አብረን መኖር እንፈልጋለን፡፡ ሆኖም እንደ ሰው እና እንደ ብሔር ያለን መብት ወይም ነጻነት እንዲከበር እንሻለን›› የሚል ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ህዝቦች በህገ መንግስታቸው አንድ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመገንባት የወሰኑትም ለዚህ ነው፡፡

ሰዎች አንድን ጥሩ ብለው የሚያስቡትን ነገር ለመፈጸም ሲሰባሰቡ ማህበረሰብን ይፈጥራሉ፡፡ በዚህ የተነሳ እያንዳንዱ ማህበረሰብ የራሱ ልዩ ባህርይ  እና ሊያሳካው የሚፈልገው ዓላማ ይኖረዋል፡፡ ኢትዮጵያውያን እንደ ህዝብ አንድ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመፍጠር ሲወስኑ፣ የብሔር ማንነት እንዲከበር ውሳኔ አድርገዋል፡፡

ታዲያ ሁሉም ማህበረሰቦች አንድ ጥሩ ዓላማን ለማሳካት የሚሰሩ ከሆነ፣ ሐገረ-መንግስት የምንለው የፖለቲካ ማህበረሰብም የሚመሠረተው ከሁሉ የላቀ ማዕረግ የሚይዝ አንድ ዓላማን ለማሳካት ነው፡፡ አንድ ሐገረ መንግስት የተለያዩ ማህበረሰቦችን አጠቃሎ የሚይዝ እና በማዕረጉ ከሁሉ የላቀ ሥፍራ የሚይዝ ዐቢይ ዓላማን ለማሳካት የሚሰራ ህብረት ከሆነ፣ የኢትዮጵያውያን ዓቢይ ዓላማ፣ አንድ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ማህበረሰብ መፍጠር ነው፡፡

በመሆኑም፣ የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች፣ አንድ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመገንባት ሲወስኑ ለከንቱ አይደለም፡፡ ህዝቦች እንዲህ ዓይነት ውሳኔ ሲወስኑ፣ ጥሩ የሚሉትን አንድ ጉዳይ ለማሳካት በመሆኑ፣ የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች፣ ‹‹የራሳቸውን በራሳቸው የመወሰን መብታቸውን ተጠቅመው፣ በነጻ ፍላጎታቸው ተመርተው፣ በራሳቸው ፈቃድ ላይ የተመሠረተ አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ በጋራ ለመገንባት ቆርጠው በመነሳት›› የኢፌዴሪ መንግስትን ሲመሠርቱ፣ የየራሳቸው አኩሪ ታሪክ እና ባህል ባህል

ያላቸው ቢሆንም፤ በተለያዩ መስኮች እና የግንኙነት ደረጃዎች ተሳስረው አብረው የኖሩ በመሆናቸው ያፈሩት የጋራ ጥቅም እና አመለካከት መኖሩን በመገንዘብ፤ ከታሪካቸው የወረሱትን የተዛባ ግንኙነት በማረም የጋራ ጥቅማቸውን የማሳደግ ዓላማ ነድፈው ነው፡፡ ጥቅማቸውን፣ መብታቸውን እና ነጻነታቸውን በጋራ እና በተደጋጋፊነት ለማሳደግ በማሳብ ነው፡፡ አንድ የኢኮኖሚ እና የፖለቲካ ማህበረሰብ የመገንባት ዓላማ ቀርጸው ነው፡፡

የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች፤ የዓላማቸው እና የእምነታቸው ማሰሪያ እንዲሆን በቀረጹት የቃል ኪዳን ሰነድ ‹‹አንድ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ማህበረሰብ›› ለመገንባት ሲወስኑ፤ በመካከላቸው ያለው ግንኙነት፤ በአንድ ከተማ እንደሚኖሩ ሰዎች ላላ ያለ ሳይሆን፤ በአንዲት መንደር እንደሚኖሩ ሰዎች ጥብቅ ቁርኝት ለመፍጠር ነው፡፡

የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች፤ የላቀ ዓላማም አንድ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ማህበረሰብ መገንባት መሆኑን በቃል ኪዳን ሰነዳቸው አስፍረዋል፡፡ ዘጠኝ ክልሎችን የሚያካትተውና ‹‹ኢፌዴሪ›› በሚል የሚጠቀሰው ‹‹የትልቁ›› ማህበረሰብ ዓላማ፤ አንድ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ማህበረሰብ መገንባት ከሆነ፤ የፌዴራሉ አባሎች የሆኑት ‹‹ንዑሳን›› ማህበረሰቦች ዓላማ ከዚህ የተለየ አይሆንም፡፡ የፌዴራሉን አባሎች ወሰን በሚያጠቃልለው የኢትዮጵያ የግዛት ወሰን የሚኖሩት ኢትዮጵያውያን ዜጎች ፍላጎትም ይኸው መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ በፌዴራሉ ህገ መንግስትም የተጠቀሰው ይኸው ነው፡፡

ሁሉም አባል ክልሎች (በመሆኑም ሁሉም ኢትዮጰውያን ዜጎች) አንድ ዓላማን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ኢፌዴሪ በሚል የሚታወቀው እና የተለያዩ ‹‹ንዑሳን ማህበረሰቦችን›› (ክልሎችን) አካቶ የሚይዘው የፖለቲካ ማህበረሰብ፤ ከሁሉ የሰፋ እቅፍ ያለው ፌዴሬሽን ሲሆን፤ ከሁሉ በላቀ መርህ ላይ ተመስርቶ፤ ከሁሉ የላቀ ዓላማን ለማሳካት የሚሰራ የፖለቲካ ማህበረሰብ ነው፡፡ ለዚህም ነው፤ የሐገሪቱ የበላይ ሕግ የሆነው የፌዴራሉ ሕገ መንግስት፤ ‹‹በፌዴሬሽኑ አባል ክልሎች ውስጥ የሚጸና ማንኛውም ሕግ፣ ልማዳዊ አሰራር፣ እንዲሁም የመንግስት አካል ወይም ባለሥልጣን ውሳኔ ከዚህ ህገ መንግስት ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈጻሚነት አይኖረውም›› (9/1) ሲል የደነገገው፡፡

የኢፌዴሪ ሕገ መንግስት፤ ‹‹በዚህ ሕገ መንግስት ከተደነገገው ውጭ በማናቸውም አኳኋን የመንግስት ሥልጣን መያዝ አይቻልም›› (9/3) ወዘተ በማለት ከሁሉ የሚልቁ ዓላማዎችን አስቀምጧል፡፡ ይህ ሕገ መንግስት፤ በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የፌዴራል እና የክልል መንግስታት (ሕግ አውጪ፣ አስፈጻሚና የዳኝነት አካላት)

ማክበር እና ማስከበር ያለባቸውን ከሁሉ የላቁ ብሔራዊ መርሆዎችን፣ ፖሊሲዎችን እና ዓላማዎችን ይዘረዝራል፡፡ የሁሉንም የሐገሪቱን ዜጎች ጥቅም የሚያስከብሩ ተቋማትን በማደራጀት፤ ከአንድ ክልል በላይ የሚሸፍኑ የአገልግሎት ተቋሞችን በማስተዳደር፤ ከአንድ ክልል የሚያልፉ ግንኙነቶችን በማጣጣም፤ አንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመፍጠር የሚያስችል መደላድል ፈጥሯል፡፡

የፌዴራሉ ሕገ መንግስቱ አንቀጽ 88፤ ‹‹መንግስት፤ በዴሞክራሲያዊ መርሆዎች ላይ በመመስረት ሕዝቡ በሁሉም ደረጃዎች ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበትን ሁኔታ ያመቻቻል›› ካለ በኋላ፤ ‹‹መንግስት የብሔሮችን፣ የብሔረሰቦችን እና የሕዝቦችን ማንነት የማክበርና በዚሁ ላይ በመመርኮዝ በመካከላቸው እኩልነት፣ አንድነትና ወንድማማችነትን የማጠናከር ግዴታ አለበት›› ሲል ይደነግጋል፡፡ ከእነዚህ ፖለቲካ ነክ ዓላማዎች በተጨማሪ፤ ሕገ መንግስቱ ‹‹መንግስት ሁሉም ኢትዮጵያውያን የሐገሪቱ የተጠራቀመ ዕውቀት እና ሐብት ተጠቃሚዎች የሚሆኑበትን መንገድ የመቀየስ ኃላፊነት አለበት›› (89/1) ሲል ይደነግጋል፡፡ እንዲሁም ‹‹ሁሉም ኢትዮጵያውያን የኢኮኖሚ ሁኔታ የሚሻሻልበትን፤ እኩል የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ዕድል የሚያገኙበትን እና ሐብት ፍትሐዊ በሆነ መንገድ የሚከፋፈልበትን ሁኔታ የማመቻቸት ግዴታ አለበት›› (89/2) ሲል ያዛል፡፡ የመሠረትነው የፖለቲካ ማህበረሰብ እንዲህ ያሉ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዓላማዎች ያሉት ማህበረሰብ ነው፡፡ ይህ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ተሰርቶ የተጠናቀቀ ሳይሆን፤ ገና ዳዴ ማለት የጀመረ በመሆኑ፤ ብዙን ፈተናዎች በማለፍ መጠናከር ይኖርበታል፡፡ አሁንም ፈተናዎች ተጋርጠውበታል፡፡

አርስጣጣሊስ ‹‹ዴሞክራሲን ከማግኘት ይልቅ፤ ጠብቆ ማቆየቱ እጅግ ከባድ ይሆናል›› ይላል፡፡ ኢትዮጵያውያን ይህን ዴሞክራሲያዊ እና ፌደራላዊ ስርዓት ለማግኘት እጅግ ብርቱ ፈተናዎችን ያለፉ ቢሆንም፤ ካለፉት ይልቅ ከፊታቸው ያለው ፈተና ከባድ ይሆናል፡፡ የአርስጣጣሊስ ብሂል የሚጠቁመን ይህን እውነት ነው፡፡

ወቅታዊ የሪፐብሊካችን ፈተናዎች ይታወቃሉ፡፡ ፈተናዎቹ በጥልቅ ተሐድሶ መድረክ ነጥረው ወጥተዋል፡፡ የሞት-ሽረት የትግል አጀንዳዎች አድርገን ይዘናቸዋል፡፡ እናም በዚህ ትግል መሸነፍ የለብንም፡፡

ከወቅታዊ ፈተናዎቹ አንዱ ‹‹የአንድ ብሔር የበላይነት አለ›› የሚል አመለካከት ነው፡፡ በርግጥ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች የመሠረቱት ፌዴራላዊ የፖለቲካ ማህበረሰብ፤ ጥቂቶች በብዙሃኑ ላይ መሰልጠን የሚችሉበት ስርዓት ባይሆንም፤ አዲሱን ስርዓት የአንድ ብሔር የበላይነት የሚንጸባረቅበት የፖለቲካ ማህበረሰብ አድርጎ የማቅረብ ሁኔታ ይታያል፡፡

እንደሚታወቀው፤ አዲሲቱን ኢትዮጵያ የሚያስተዳድረው መንግስት ግለሰባዊ የዘውድ መንግስት አይደለም፡፡ በአንድ ግለሰብ ቃል የሚመራ አምባገነናዊ መንግስትም አይደለም፡፡ ይህ መንግስት በዴሞክራሲያዊ መርሆዎች ላይ የተመሰረተ፤ ዜጎች በቀጥታ እና በውክልና ተሳትፎ የሚያደርጉበት፤ ዜጎች በጋራ እና በተናጠል በጉዳዮቻቸው እየመከሩ ራሳቸውን በራሳቸው ማስተዳደር የሚችሉበት ፌዴራላዊ መንግስት ነው፡፡

ስለሆነም፤ የብዙሃኑን ድጋፍ ያገኘ ሐሳብ፤ ፖሊሲ እና ሕግ ሆኖ እየተቀረጸ፤ ዜጎች ራሳቸውን በራሳቸው በሚያስተዳድሩበትና በዴሞክራሲያዊ መርህ የታነጸ ሪፐብሊካዊ መንግስት ነው፡፡ በዚህ ውስጥ የአንድ ብሔር የበላይነት የሚረጋገጥበት ዕድል አይኖርም፡፡ ሆኖም አንዳንዶች የኢትዮጵያ መንግስት የአንድ ብሔር ወይም ድርጅት የበላይነት የተረጋገጠበት መንግስት እንደሆነ ሲናገሩ ይሰማል፡፡ በመሆኑም ይህ ጉዳይ ጥናት እና ውይይት ሊደረግበት ይገባል፡፡